# እኛ የቤተ ክርስቲያን ልጆች እስከመቼ ከሀገራችን ፖለቲካ ጋር ማዶ ለማዶ እንደተያየን እንኖራለን???

*በፍቅር ለይኩን ~ከደቡብ አፍሪካ*
*fikirbefikir@gmail.com*

ለዛሬ ጹሁፌ መነሻ የሆነኝ በዚህ በደቡብ አፍሪካ በሚገኘው በኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በጆሐንስበርግ ጽርሐ ጽዮን መድኃኔ ዓለም ካቴድራል የሚያገለግሉ የደቡብ አፍሪካዊነት ዜግነት ያላቸው ዕድሜያቸው ወደ 70ዎቹ የተጠጋ አዛውንት ካህን በሀገር አቀፍ ደረጃ ለሚካሄደው (Local Government Election) ከሚያገለግሉበት ከጆሐንስበርግ መድኅኔ ዓለም ቤ/ን ከአንድ ሺ ኪሎ ሜትር በላይ ወደ ሚርቀው ትውልድ መንደራቸው ድምጽ ለመስጠት እንደሚሄዱ ሲያጫውቱኝ በጣም በመገረም ሆኜ፡-

ፋዘር ዴሊዛ እንዴት ድምጽ ለመስጠት ብለው ይሄን ያህል ኪሎ ሜትር አቋርጠው ይሄዳሉ፣ ለምንስ ብለው ይሄን ያህል ብር ለመጓጓዣ ያወጣሉ በማለት በመገረም ለጠየኳቸው ጥያቄዬ ሲመልሱልኝ፡-

> እንዴ ለፓርቲዬ ሽንፈትም ሆነ ውጤት የእኔ ድምጽ ዋጋ እንዳለው አታውቅም እንዴ...? ደግሞም እኔም ሆንኩ የቀደሙ ወንድሞቼ የታገልነው ለዚህ ነጻነትና መብት እኮ ነው...!? ዛሬ ለዘመናት ስንናፍቀው የነበረው ከእናት ኦርቶዶክሳዊት ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያናችን ጋር እንዳንገናኝ ዘረኛው የአፓርታይድ መንግስት የጫነብንን የባርነት ቀንበር ሊሰብር የቻልነውና ይሄን መብት የተጎናጸፍነው የቀደሙት የነፃነት አርበኛ ወንድሞቼ በከፈሉት ውድ የሕይወት መስዋዕትነት ጭምር ነው። ስለዚህም ይሄን መብቴን መጠቀም ይኖርብኛል ልጄ በማለት ለዚህ ክቡር ነፃነት ላበቃቸው ፓርቲያቸው ድምጻቸውን ላለመስጠት የትውልድ ቀዬያቸው ርቀትና የሚያወጡት የትራንስፖርት ገንዘብ የእንደማያግዳቸውና በብዙ ደምና መስዋዕትነት የተገኘ ይሄ መብትና ነፃነት በቦታ ርቀትና በገንዘብ ሊለካ እንደማይችል ነግረውኝ ተለያየን።

እኚህ የዕድሜ ባለጸጋ ካህን ስለ መምረጥ መብታቸውና ነፃነታቸው ያሉኝን እያሰብኩ ወደ ራሴ ፖለቲካዊ ተሳትፎና በሀገራችን ስላለው የመምረጥና የመመረጥ መብት፣ ከምርጫ በፊትና ማግስት ስላሉ ትርምሶችና ዝብርቅርቆች ሳስብ፣ እንዲሁም በሀገራችን ዲሞክራሲያዊ ሥረዓት፣ ፍትህና ነፃነት እንዲሰፍን ያለን ቁርጠኝነትና እንዲሁም ስለ ነፃነታችንና ሰለ መብታችን ያለን ፖለቲካዊ ግንዛቤ (Political Consciousness) አናሳ መሆኑ በተለይም ደግሞ ስለ ነፃነት ክብር በእጅጉ ጎልቶ በሚነገርባትና ክርስቲያኖች በምድር ላይ ፍትህን በማሰፈን የባርነትን ቀንበር መሰበርና አርነትን ማወጅ እንደሚገባቸው በወንጌል ቃል ከምታስተምር ቤተ ክርስቲያን የወጣን የኦርቶዶክሳዊት ተዋህዶ ቤ/ን ልጆች በዲሞክራሲያዊ ሥረዓትና ፍትህ ዙሪያ ስለ ራስችንም ሆነ ስለሌሎች ነፃነትና መብት መከበር ድምፃችንን ለማሰማት ያለን ወኔ ከእኚህ በቤተ ክርስቲያናችን እያገለገሉ ካሉ ደቡብ አፍሪካዊ ካህን አዛውንት አንፃር ሳየው በጣም የወረደ እንዳንዴም የሌለ መስሎ ቢሰማኝ ይህችን ጹሁፍ ለመጻፍ ተነሳሳሁ። ስለዚህም በጣም በአጭሩ የዘመናዊን የሀገራችንን ፖለቲካ ጅማሬ ሂደትና የዲሞክራሲያዊ ሥረዓት ግንባታ ውጣ ውረዶች፣ እንዲሁም ክርስቲያኖች በዚህ ዙሪያ ሊኖራቸው ስለሚገባው ተሳትፎ ከሌሎች ሀገሮች ልምድ በመጥቀስ የተሰማኝንና የበኩሌን ለማለት ወደድሁ።

ትዝ ይለኛል በአቅራቢያችን በሚገኝ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ት/ቤት ተማሪዎች በነበርንበት በአንድ ወቅት ከሰንበት ት/ቤት አግልግሎትና ከቤተ ክርስቲያን አለወትሮው አብዝቶ መጥፋት የጀመረውን አንድ ወንድማችንን ለመጎብኘት በማሰብ ሰብሰብ ብለን ወደ ቤቱ አመራን። ወደ ቤቱ እንደ ደረስንም ሰላምታ ተለዋውጠን አረፍ ብለን ሻይ ቡና እያልን በመጫወት ላይ እያልን ከእኛ መካከል አንዱ ወንድማችን ከቤተ ክርስቲያንና ከሰንበት ት/ቤት አግልግሎት አብዝቶ የጠፋበትን ምክንያት በጨዋታችን መሀል ለዚህ ወንድማችን ላነሳው ጥያቄ ይኸው ወንድማችን ሲመልስ፦

"እንዴ! ዘንድሮ የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና እንደምወስድ ታውቃላችሁ አይደል!? እናም ብዙ ጊዜዬን ለጥናት ነው የማውለው፤ በርትቼ አጥንቼ ዩኒቨርስቲ መግባት እፈልጋለሁ... አያችሁ እኛ ክርስቲያኖች በርትተን ተምረን በሀገራችን በሚገኙ የፖለቲካ፣ የማኅበራዊና የኢኮኖሚ ተቋማት ውስጥ ወሳኝ ሚና መጫወት ይገባናል። በፍትህ እጦት፣ ቅንነት በጎደለው አስተዳደር፣ በሙስናና በጉቦ ለሚማረረው ወገናችን እኛ ክርስቲያኖች በርትተን ተምረን ልንደርስለት ካልቻልን ማን ሊመጣለት ይችላል...?" በማለት በዛ አፍላ ዕድሜያችን ብዙ ያላሰብንበትን እሱን ግን የቆጨውን ጉዳይ በማንሳት... ለዚህም ክርስቲያኖች ወሳኝ በሆኑት የሀገሪቱ ፖለቲካና እኮኖሚያዊ ተቋማት ደፍረው መምጣት እንዳለባቸው በዛን በአፍላ የወጣትነታችን ዘመን ያካፈለን ቁም ነገር ዛሬ ላይ ሆኜ ሳስበው በውስጤ አንድ እውነታ ጫረብኝ።

እናም በእርግጥስ የቤተ ክርስቲያን ልጆች በሀገሪቱ ፖለቲካዊ ተቋማት ውስጥ መጫወት የሚችሉት ሚና ምን መሆን አለበት ብዬ ራሴን ለመጠየቅ ፈለግሁ፤ ይሄን ጥያቄ በማንሳት ወደ አህጉራችን አፍሪካና ወደ ሌሎች የዓለማችን አንዳንድ ሀገሮች የክርስቲያኖች ፖለቲካዊ ተሳትፎ ምን እንደሚመስል ለማየት ስሞክር፤ እኛ ምን ያህል ከሀገራችን የፖለቲካ እውነታ እና ፖለቲካዊ ተሳትፎ በጣም በርቀትና መሰረት በሌለው ፍርሃት ተቀፍድደን እንዳለን ሆኖ ተሰማኝ፣  ያም ብቻ ሳይሆን "ፖለቲካንና ኤሌትሪክን በሩቁ ነው" የሚለው ባለቤትና እውነታ የሌለው የዋህኖች ተረት ምን ያህል ለፖለቲካው ዓለም ሥነ ልቦናዊ ጫናና ፍርሃት እንዳሳደረብን ስረዳ በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ አብዝተን መነጋገር እንዳለብን ተሰማኝና የድርሻዬን ለማለት ብዕሬን አንሳሁ። በእርግጥ በሀገራችን የፖለቲካው ሜዳ ጠባብና ብዙ ማስፈራሪያ ዛቻና መከራን የተሞላ መሆኑ እውነት ቢሆንም ያለመስዋዕትነት ድል የለምና የፖለቲካው ሜዳውን የተደላደለ ለማድረግ በእጅጉ ቁርጠኝነት ያስፈልገናል።

አለመታደል ይሁን የታሪክ አጋጣሚ የሀገራችን የዘመናዊ ፖለቲካ ጅማሮ አሃዱ የተባለው በሙሉ ማለት ይቻላል ግራ ዘመም በሆኑ የማርክሲስት ፍልስፍና እና የሶሻሊስቱን ዓለም የፖለቲካ እሳቤ በተቀበሉ፣ ክርስትና ወይም መንፈሳዊነት አሊያም ሃይማኖት ድሆች ለመጽናኛ ሲሉ የፈጠሩት ከንቱ ሞኝነት ነው በሚል የእግዚአብሔርን ህልውና በሚገዳደሩ ሰዎች ፍልስፍና ስር የወደቀ ነበር የሀገራችን የወቅቱ ፖለቲካ እንቅስቃሴ፤ በዚህም የተነሳ በሶሻሊስቱ አብዮት የተጠመቁ አብዛኞቹ ሀገራትም ሆኑ ህዝቦች እግዚአብሔር በሰዎች ማኅበራዊም ሆነ ፖለቲካዊ ሕይወት ምንም ስፍራ የሌለው ምናባዊ ቅዠት እንደሆነ በሚታሰብበት በዛ ወቅት ክርስቲያኖችም ሆኑ ክርስትናው በፖለቲካው መድረክ በጣም የሚጠሉና የሚገፉ ነበሩ።

ይሄን ሐሳቤን የሚያጠናክርልኝ አንድ ገጠመኝን ልጥቀስ፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተማሪ በነበርኩበት ጊዜ በSchool of Journalism and Communication ረዳት ፕሮፌሰር የነበሩ የCommunication skill አስተማሪያችን በወቅቱ በ1997ቱ ድኅር ምርጫ በሀገሪቱ ላይ የተከሰተው ያ ቀውጢ ቀን አልፎ ወደ ትምህርት ገበታችን ከተመለስን በኃላ በሆነው ነገር ያዘኑት እኚህ መምህራችን በዳመነ ስሜት ወደ ኃላ ወደ ራሳቸው ዘመን የአብዮት ወቅት በመሄድ በ1960ዎቹ የኃይለ ሥላሴን የዘውድ መንግስት ለመጣል በሚያደርጉት ትግልና ፀረ

ሃይማኖት በሆነው አብዮት እንቅስቃሴ የተከሰተውን ገጠመኛቸውን ከወቅቱ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ሂደት ጋር በማያያዝ እንዲህ በማለት አጫወቱን።

በቀ.ኃ.ስ ዩኒቨርስቲ በአሁኑ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ 6ኪሎ ካምፓስ እኚህ መምህራችን ጭምር ተሳታፊ በነበሩበት ልደት አዳራሽ ውስጥ ሲካሄድ በነበረ በአንድ ስብሰባ ላይ ተማሪዎች በጋለ ስሜትና ወኔ አዳራሹ በኮሚኒስታዊ መፍክርና ጩኸት በሚናወጥበት አጋጣሚ አንድ ተማሪ ድንገት በመነሳት እጁን በማጨብጨብ የብዙዎቻችንን ትኩረት ለማግኘት ሲል አዲስ ዜና አለኝ አለ ድምፁን ከፍ በማድረግ፤ ከአፍታ በኃላ የአዳራሹ ተማሪ ቀልብ በሙሉ ወደ እሱ መሆኑን የተረዳው ተማሪ ድምፁን ከፍ በማድረግ እንዲህ ሲል ተናገረ፡-

"ወንድሞቼና እህቶቼ ለውጥ እጅግ አስፈላጊ መሆኑን ባምንም አሁን በያዝነው መንገድ ግን የፈለግነው ለውጥ ሊመጣ የሚችል አይምስለኝም፤ መጽሀፍ ቅዱስ ሰለ ሰው ልጆች ነፃነትና ስለ ፍትህ አበክሮ ይናገራል። ህዝባቸውን ከባርነት ቀንበር ስለታደጉና ነፃ አውጭ ስለነበሩት ሙሴ፣ ኢያሱ፣ ዕዝራ ስለሌሎችም የነፃነት አርበኞች ነቢያት ይናገራል፣ ግን አሁን እኛ በያዝነው እግዚአብሔር የለሽ ሶሻሊስታዊ አብዮት እና ነውጥ ለውጥም ሆነ ነፃነት የሚታሰብ… ስለዚህም…" ተማሪው ንግግሩን አልጨረሰም በአንድ ድምጽ ሁላችንም ስቀለው! ስቀለው! በማለት ዳግም እንደገና አዳራሹን በማናውጥ ይሄን የጊዜውን ነቢያትና ፍልስፍና ሚያቃልል ኮምፓሱ የጠፋበት ሰባኪ ነኝ ባይ ተማሪ እየገፈታተርን ከአዳራሹ እንዲወጣ ያደረጉበትን ገጠመኝ ከነገሩን በኃላ በቁጭት ውስጥ ሆነው ያ ክርስትናን እንደ ከንቱ ነገር ያቃለለው፣ ብዙ የተባለለትና ተስፋ የተጣለበት አብዮት የሚበዙት ባልንጀሮቻቸውን ጭምር ሳይቀር የበላበትን መጥፎ ትዝታቸውን እንዲህ ቀጠሉልን፡-

"ከዓመታት በኃላ ያ እንዲያ የጮህንለት የሚበዙት ጓደኞቻችን የሕይወት መስዋዕትነት ሳይቀር የከፈሉበት ተስፋ ያደረግነው አብዮታችን በሂደት ለእኛም ሆነ ለህዝባችን የማያባራ የመከራ ዶፍ፣ ስደት፣ እንግልትና ሞት ብቻ እንዳተረፈልን ሳስበው…" በማለት መምህራችን ትናት የሆነውን ዛሬም ቀጥሎ ያለውን የእርስ በርስ የመበላላትና የመጠፋፋት የሀገራችንን የፖለቲካ ሂደት ላይ በመቆዘም በምናባቸው በታሪክ ሰረገላ ወደ ኃላ በሃሳብ ነጎዱ…

እርግጥም በዚህ አቅጣጫ የተጀመረው ዘመናዊ የሀገራችን የፖለቲካ ለውጥ ጉዞ እንዳርጋቸው ጽጌ የተባሉ ፖለቲከኛና ጸሐፊ 'ነጻነትን የማያውቅ ነጻ አውጭ' በሚል መጽሀፋቸው እንደገለጹት "መንገዱ በደም ርሶ፣ በአሳርና በመከራ ታርሶ ህዝብ ከተቀፈደደበት የድህነትና የባርነት ቀለበት ሳይሰበር ካለንበት ዘመን ደርሰናል፤ ሌላው ቀርቶ ተመሳሳይ የሆነ የለውጥ አቅጣጫ የተከተሉ ሌሎች ሀገሮች ሊያከናውኑ የቻሉትን፣ ህዝብ ሳይራብ የሚኖርበትን ሁኔታ መፍጠር አልቻልንም፣ ከነገስታቱ ዘመን የቀጠለው ዶፉ ዛሬም ያላባራው የህዝብ መከራና ሲቃ የሚዘንበው ከእዚያው ከትናቱ የጨለማ ሰማይ ነው።" በማለት ያ ትውልድ ከከፈለው ግዙፍ መስዋዕትነት አንጻር ሲታይ የተባለው ለውጥና ዲሞክራሲያዊ ሥረዓት ዛሬም ገና በሁለት እግሩ መቆም አቅቶት እየተንፏቀቀ እንዳለ ትዝብታቸውን አስፍረዋል።

በእርግጥም በእግዚአብሔር የለሹ አብዮት ህዝቦችም ሆኑ ሀገራት ያተረፉት መከራን፣ ሞትን አሰቃቂ የሆነ ድህነትንና መሰደድን እንደሆነ ታሪክ ህያው ምስክር ነው። በእግዚአብሔር የለሹ ኮሚንስታዊ ሥረዓት የተፈጠረው የደርግ መንግስት አብያተ ክርስቲያናት ወደ ህዝብ ሙዜየምነት ይቀየራሉ፣ ተፍጥሮን በቁጥጥራችን ሥር እናውላለን፣ ሃይማኖት ሰፊውን ህዝብ ማድንዘዣ ዕፅ ነው… በሚሉ የተውሶ መፈክሮችና እሳቤዎች ሀገሪቱ አኬልዳማ በሆነችበት፣ በርካታ የሃይማኖት አባቶች በተሰደዱባት፣ በተጋዙበትና በተገደሉባት ኢትዮጵያ የ1966ቱ አብዮት ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ያመዘነበትን የጨለማ ዘመን ታሪክ በሀገራችን ትቶ አልፏል።

እንደ ፈጣሪ ሲታዩ በነበሩት ቀንደኛ የኮሚኒስት ሥረዓት አራማጅና አቀንቃኝ ሀገራት ለምሳሌ ያህል በግንባር ቀደምትነት የሥረዓቱ ተጠሪ በነበረችው የቀድሞዋ ሩሲያ የብዙ ትውልድን ታሪክና ቅርስ በብዙ ተጋድሎና መስዋእትነት ያቆየችው የራሺያ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማቶቻቸው የብዙ ትውልድን ቅርስ ከያዙበት ታሪካቸውና ባህላቸው ጋር እንዲወድሙና እንዲዘጉ የተደረገበት የታሪክ አጋጣሚ ከቀዝቃዛው ጦርነት ማብቂያ ማግስት በኃላ የቀድሞዋን ሩሲያ ብሔራዊ ማንነት፣ ባህልና ታሪክ ለመመለስ በእልህና በቁጭት ብዙዎች ደፋ ቀና ያሉበትንና ኮሚኒስታዊው ሥረዓት በረጅሙ ዘመን ታሪካቸውና ቅርሳቸው ላይ ያደረሰውን ውድመት ብዙዎች በሀዘንና በዕንባ ጭምር እንዲያስቡት ያደረገበትን የታሪክ አጋጣሚ ለመታዘብ በቅተናል።




ከዚህ ቁጭታቸውና ሀዘናቸው በኃላ ቤተ ክርስቲያኒቱ በወሰደችው ቁርጥ አቋም የቤተ ክርስቲያኒቱ ወጣቶች በሀገሪቱ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ተቋማት ውስጥ ወሳኝ የሆነ ሚና እንዲጫወቱ በማበረታትና የአገሪቱን ብሔራዊ ማንነት ታሪክና ቅርስ በመጠበቅ በሰፊው ተንቀሳቅሳ ነበር፣ በሀገሪቱ የሚገኙ ታላላቅ ፖለቲከኞችና የምክር ቤት አባላት ቆፍጣናውን መሪ ፕሬዝዳንት ፑቲንን ጨምሮ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የድካም ውጤቶች መሆናቸውን ልብ ይሏል።

በእኛስ ሀገር መቼ ይሆን የቤተ ክርስቲያን ልጆች በሀገሪቱ ወሳኝ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ተቋማት ውስጥ በብዛት ለማየት የምንታደለው፣ መቼ ይሆን "ፖለቲካንና ኤሌትሪክን በሩቁ ነው" ከሚል አጉል ብሂል ወጥተን ለሀገራችን ብሔራዊ ጥቅም፣ ለዲሞክራሲያዊ ሥረዓትና ለመብታችን የምንታገለው? መጽሀፍ ቅዱስ በምሳሌ መጽሀፍ ላይ፡-

አፍህን ስለዲዳው ክፈት፣ ተስፋ ስለሌላቸውም ሁሉ ተፋረድ። አፍህን ክፈት፣ በእውነትም ፍረድ፤ ለድሃና ለምስኪን ፍረድ።" በማለት ይናገራል፤ በሌላ ሥፍራም የእግዚአብሔር ህዝቦች እሥራኤላውያን በአምላካቸው ፊት ስላቀረቡት መስዋዕትና ስለፆማቸው ተቀባይነት ማጣት ሲሟገቱ በነቢዩ ኢሳይያስ በኩል የአባቶቻቸው አምላክ እንዲህ በማለት ነበር ጥያቄያቸውን በጥያቄ የመለሰላቸው፡-

". . .እኔ የመረጥሁት ጾም ይህ አይደለምን? የበደልን እስራት ትፈቱ ዘንድ፣ የቀንበርንስ ጠፍር ትለቁ ዘንድ፣ የተገፉትንስ አርነት ትሰዱ ዘንድ፣ ቀንበሩንስ ሁሉ ትሰብሩ ዘንድ አይደለምን?..." ኢሳ ፶፰፥፮፥፲፬ ስለዚህም እንደ አምላካችን እግዚአብሔር ቅዱስ ቃል በባርነት ቀንበር ስር ስለወደቁት፣ መብታቸውንና ከፈጣሪ የተሰጣቸውን ነፃነታቸውን ለተገፉ ሁሉ እንጮህላቸውና እንሟገትላቸው ዘንድ የእኛ የክርስቲያኖች ኃላፊነትና ብቻ ሳይሆን ግዴታም ጭምር ነው። ፆማችንና ጸሎታችን ትርጉም የሚኖረው ለተገፉና ለድሆች ፍትህን በማድረግ የተጫነባቸውን የባርነት ቀንበር መስበር ስንችል ነው።

አለበለዚያ ግን እንደቀደሙት የአባቶቻችን ዘመናት "ንጉሥ የወደደውን ዘመን የወለደውን" ሰጥ ለጥ ብልህ ተቀበል ከሚሉ አስመሳዮችና ሆዳቸው አምላካቸው የሆነ፣ የወንጌልን ቃል ከሚሸቃቅጡ እግዚአብሔር የለሾች፣ በህዝባቸው ላይ የተጫነውን የመከራና የባርነት ቀንበር በማጥበቅ በእግዚአብሔር ስም ህጋዊነት ለመስጠት ከሚደክሙ የቀበሮ ባህታውያንና ጥቅመኞች (Opportunists) ዓይነት አስተሳሰብ ሰብረን ወጥተን በሌሎች ሀገራት በሰላማዊ ትግል መድረክ የሀገራቸውን የፖለቲካ ሥረዓት ከለወጡ እግዚአብሔርን የሚፈሩ ህዝባቸውን

የሚያከብሩና የሚያፈቅሩ፣ ለህዝባቸው መብትና ነጻነት ነፍሳቸውን እንኳ ለመስጠት እንዳልሳስሱት እንደ፡- ዶ/ር ማርቲን ሉተር ኪንግ፣ ታላቁ ነፍስ በመባል በሚጠሩት የህንዳውያን የነፃነት አባት ማህተመ ጋንዲ፣ አፍሪካዊው የነፃነት አርበኛ፣ የይቅርታና የሰላም አባት ኔልሰን ማንዴላ ዓይነት ወሳኝ የሆነ ፖለቲካዊ ሚና መጫወት እንዳለብን ይሰማኛል እኛ ክርስቲያኖች።

ስለ ራስም ሆነ ስለሌሎች መብት በሰላማዊ መንገድ መታገል፣ ልፍትህና ለነፃነት መቆም



በምንም ዓይነት መንገድ ስህተት ሊሆን አይችልም፣ በክርስትና ሕይወታችን ለፍትህና ለነፃነት ያለንን ቀናዒነትና ቁርጠኝነት በሁሉም አጋጣሚ ልናሳይ ይገባናል። በአንድ ወቅት አሜሪካዊው የስብዓዊ መብት ታጋይና ሰባኪ ወንጌል ማርቲን ሉተር በአላባማ ከተማ ስለ ጥቁር ህዝቦች ነፃነትና መብት መከበር ባደረገው ንግግር እንዲህ ነበር ያለው፡-

> We are not here to advocating violence... I want to be known through out Montgomery and through this nation that we are Christian people... the only weapon that we have in our hands this evening is the weapon of protest... for what we are doing is right. What we are doing is just- and God is with us. If we are wrong, the constitution of the United States is wrong...if we are wrong, justice is a lie...

የዛሬዋ አሜሪካ ብልጽግና፣ ፍትህ፣ ዲሞክራሲያዊ ሥረዓትና የሰው ልጆች መብትና ነፃነት መሰረት የቀደሙ አባቶቻቸው የሀገራቸውን ህልውና በመጽሀፍ ቅዱስ እውነታ ላይ በመመስረታቸው ነበር፤ ለሰው ልጆች የማይገሰስ ነፃነት ክብር የነበራቸውና አምርረው የታገሉ የትናትናዋ አሜሪካ የቁርጥ ቀን ልጆች ለነፃነታቸውና ለመብታቸው ክቡር ሕይወታቸውን ጭምር ለግሰው ነው ያለፉት።

ዛሬ በአሜሪካን ታሪክ ጥቁር መሆን እንደ ወንጀል የሚታይበት ጨለማው የታሪክ ዘመን አልፎ በአሜሪካ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ጥቁር ፕሬዝዳንት በመሆን ባራክ ኦባማ ወደ ነጩ ቤተ መንግስት ለመግባት ቃለ መሃላ ባደረገብት ጊዜ ብዙ አፍሪካውያንና አፍሪካ አሜሪካውያን በደስታ አንብተዋል፤ እንኳን ፕሬዝዳንት ለመሆን ቀርቶ 1/16ኛ የጥቁር ደም ያለው ሰው ወደ ነጩ ቤተ መንግስት መግባት አይደለም ደጁን እንኳ መርገጥ የማይችልበት ዘግናኝ የታሪክ ምዕራፍ የተዘጋበት፣ የእነ ማርቲን ሉተርና የአጋሮቹ ህልም እውን የሆነበትንና ፕሬዝዳንት ባራክ ኦባማም በበዓለ ሲመቱ ላይ ባደረገው ንግግር የቀድሞ አባቶቹ እልህ አስጨራሽ የጥቁር ህዝቦች ትግል ፍሬ አፍርቶ ሀገሩ ለዚህ አዲስ የታሪክ ምዕራፍ በመብቃቷ ደግሞ ደጋግሞ God Bless America! በማለት ደስታውንና ምስጋናውን ለአምላክ ያቀረበበትን ንግግሩን እኛም ኢትዮጵያውያን በሐሴትና በልዩ ደስታ ሆነን በቴሌቪዥን መስኮቶቻችን ተከታትለናል።

አሜሪካውያን ባለስልጣናትና ፖለቲከኞች በንግግሮቻቸውም ሆነ በሥራቸው ስም እግዚአብሔርን መጥራት ለረጅም ዘመን እንደ ባህል አድርገው የያዙት ነገር ነው፤ የመጀመሪያው የአሜሪካ ፕሬዝዳንት የነበሩት ጆርጅ ዋሽንግተን በአንድ ወቅት ለህዝባቸው

ባደረጉት ንግግርም እግዚአብሔር ለህዝባቸው ፍቅርንና አንድነትን እንዲሰጥ የተማጸኑበት ጸሎት ይህን ይመስላል፦

> "Almighty God, we make our earnest prayer that thou wilt keep these United States in Thy holy protection, that Thou wilt incline the hearts of the citizens to cultivate a spirit of subordination and obedience to government, to entertain brotherly affection and love for one another..."

በምዕራቡም ዓለም ሆነ በአሜሪካ መንግስታትና ባለሥልጣኖች በግልጽ በሃይማኖት ተቋማቶቻቸው ውስጥ በመገኘት ቡራኬ ይቀበላሉ፣ ለሚመሩት ህዝባቸውም ጸሎት ያደርጋሉ ከቤተ እምነቶቻቸው መእምናን ጋር በቅርብ ይገናኛሉ፣ ይወያያሉ። በዚህ ባለሁበት በደቡብ አፍሪካም እንደታዘብኩት የሀገሪቱ መሪዎችም ሆኑ የፓርላማ አባላት ንግግራቸውን ሲከፍቱ ስመ እግዚአብሔርን ጠርተው እንደሆነ ታዝቤያለሁ፣ ባለሁበት ዩኒቨርስቲና በሌሎች በደቡብ አፍሪካ በሚገኙ ዩኒቨርስቲዎችም እንደታዘብኩት የተማሪዎች የምርቃት ዝግጅት የሚከፈተው በጸሎት ነው። ወደ እኛ ሀገር እውነታ ስንመለስ ከ 1966 አብዮት በኃላ ስመ እግዚአብሔር ከባለሥልጣኖቻን አንደበት፣ ከትምህርት ተቋማቶቻችንና ከሀገራችን ፖለቲካ መድረክ የተገፋ እንደሆነ ቀጥሎ ያለበት ሁኔታ ላይ እንገኛለን።

የበፊቶቹም ሆነ የአሁኖቹ የሚበዙት ፖለቲከኞቻችንና ባለሥልጣኖቻችን በግልጽ በቤተ እምነታቸው ተገኝተው ለራሳቸውና እንዲሁም ህዝባቸውን የሚመሩበት ጥበብና ማስተዋል ይሰጣቸው ዘንድ ጸሎት ለማድረግ ቀርቶ ተሳስስተው እንኳ ስመ እግዚአብሔርን ከጠሩ በእፍረት የሚሽማቀቁ እንደሆኑ በብዙ አጋጣሚዎች ለመታዘብ ችለናል። ምናልባትም ብዙዎቹ ፖለቲከኞቻችን የትናት የማርክሲስት አብዮት ውጤት በመሆናቸው ይሆን... ወይስ በሌላ ምክንያት...???

የእኛ ትውልድ ከእግዚአብሔር የሆነ ጥበብና ማስተዋል ለራቀው እግዚአብሔር የለሽ ፖለቲካችን ትንሳኤ ለመሆን "ፖለቲካንና ኤሌክትሪክ በሩቁ ነው" ከሚል የሞኞች ፈሊጥ ወጥተን እንደ አስፈላጊነቱ በሀገራችን ፖለቲካ ውስጥ ያለንን ተሳትፎ ለማጠናከርና ለራሳችንና ለሌሎች መብትና ነፃነት ለመታገል የቤተ ክርስቲያንን ልጆች በብርቱ ልናስብበት ይገባናል፤ የቤተ ክርስቲያን ልጆች ፍትህ እና ብልጽግና እንዲሰፍን እጅ ለእጅ ተያይዘን መስራት ይገባናል፤ የሌሎችን እምነት ተከታዮች መብትና ነፃነት በማይነካ መልኩ በአንድነትና በመከባበር ለዘመናዊ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትና ለህዝቦች መብት መከበር በሌሎች ሀገራት እንደሆነው ሁሉ እኛም ክርስቲያኖች በሀገራችን ፍትህና ዲሞክራሲያዊ ሥረዓት ይሰፍን ዘንድ ባለንበትና በተሰማራንበት ቦታ ሁሉ የበኩላችንን ጥረት ማድረግ ይኖርብናል። እስቲ ለሎችም በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ እንፃፍ፣ እንነጋገር፣ እንወያይ...።

ሠላም! ሻሎም!